መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች

# ምርኮኛው ዳንኤል፡፡



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Jonathan Hay

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Mary-Anne S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ዳንኤልና ሶስት ወዳጆቹ በእስራኤል ይኖሩ ነበረ፡፡ አንድ ቀን ታላቅ ንጉሰ ወደ ምድራቸው መጣና ጠቢባን የሆኑ ወጣት ልጆችን ከሐገራቸው አወጣቻቸው፡፡ ንጉሱም ናቡከደነጾር ይባል ነበረ ፤ ባቢሎንም በሚባል በሩቅ አገር ይኖር ነበረ፡፡



ወጣቶቹ ልጆችም በባቢሎን በጥሩ ሁኔታ እንክብካቤን ያገኙ ነበረ፡፡ ንጉሱ ፣ እጅግ አስደናቂ አዕምሮ የነበራቸውን ወጣት ልጆች ከየአለማቱ ይመርጥ ነበረ፡፡ በባቢሎን ቋንቋ እያሰለጠናቸው የእርሱ አገልጋዮች በማድረግ ንግስናውን እንዲያግዙ ያደርጋቸው ነበረ፡፡



ምግቡም እጅግ መልካም ነበረ ። ወጣቶቹ ልጆች ንጉሱ ከሚበላው ይመገቡ ነበረ። ዳንኤልና ጓደኞቹ ግን ከዚያ መብል አይበሉም ነበረ ፤ ምክንያቱም ለሐሰተኛ አምላክ የተሰዋ ነበረና። ዳንኤል ግን አምላኩን ላለመበደል ለራሱ ቃል ገብቶ ነበረ። የእስራኤል አምላክ ሕዝቡን ከጣኦታት እና ከሐሰተኛ አማልክትጋ የተያያዘ ምንም ነገር እንዳያደርጉ አዟቸው ነበረ።



ዳንኤልም ያሰለጥናቸው የነበረውን ሰው ይቀርብላቸው የነበረውን ምግብ ለንጉሱ ከሚቀርበው ምግብ ላለመብላት እንዲፈቀድለት ጠየቀው፡፡ ንጉሱም ይሔንን ሲያውቅ እጅግ ተበሳጨ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በዚህ ሰው ፊት ዳንኤልን ተወዳጅ አድርጎት ነበረ፡፡



እርሱም ዳንኤልንና ጓደኞቹን እንዲፈትን ተስማማ፡፡ ለአስር ቀናትም አተክልትና ውኃ ብቻ እንዲወስዱ አደረጋቸው፡፡ ከአስሩ ቀንም በኋላ ዳንኤልና ጓደኞቹ ከተቀሩት የንጉሱን መብል ይበሉ ከነበሩት ወጣቶች ሁሉ እጅግ የተሻሉ ጤነኞች ሆነው ታዩ፡፡ በዚህም ምክንያት በዚሁ በአትክልትና በውኃ ብቻ እንዲቀጥሉ ተፈቀደላቸው፡፡



እነዚህ ወጣት ልጆችም እግዚአብሔርን አከበሩት ፤ እግዚአብሔርም አከበራቸው፡፡ በትምሕርታቸውም እግዚአብሔር ጥበብና እውቀትን ሰጣቸው፡፡ ዳንኤልም ራእዮችንና ሕልሞችን ሁሉ ይፈታ ዘንድ ጥበብን ሁሉ አገኘ፡፡





ከሶስት ቀናት ትምሕርት በኋላ፣ ሁሉም ወጣት ልጆች በናቡከደነጾር ፊት ቀረቡ፡፡ እርሱም ዳንኤልንና ሶስት ጓደኞቹን ከሁሉ በተሻለ ማንነት አገኛቸው፡፡ በእርግጥ ፣ ዳንኤል በአገዛዙ ካሉ ሁሉ እጅግ የተሻለ ጠቢብ እንደሆነ ንጉሱ አወቀ፡፡

አንድ ሌሊት ንጉሱ ሕልምን አለመ፡፡ አስማተኞች ፣ ኮከብ ቆጣሪዎችና ጠንቋዮች ወደ እርሱ እንዲመጡ እና በፊቱ እንዲቆሙ አዘዛቸው፡፡ ንጉሱም እንዲህ አለ ፣ “እኔ ሕልምን አለምሁ ፤ ነፍሴም የሕልሙን ትርጉም ለማወቅ እጅግ ተጨነቀች፡፡”ጠቢቡ ሰውም መለሰ ፣ “አ! ንጉስ ሆይ ለዘላለም ንገስ! ለአገልጋዮችህ ስለ ሕልሙ ንገራቸው ፣
ትርጉሙ ምን እንደሆነ እንነግርሃለን፡፡”



ንጉሡም መለሰ ፣ "በፍጹም! ያየሁትን ሕልምና ፍቺውንም ጭምር ራሳችሁ መናገር አለባችሁ።" ንጉሡም ቀጠለና ፣ "እናንተም ስጦታ ፣ ሽልማትና ታላቅን ክብር ታገኛላችሁ።" በእርግጥ ፣ ከጠቢባኑ መካከል አንዳቸውም የንጉሡን ሕልም መናገር አልቻሉም።



የንጉሱ ጠቢብም ለንጉሱ እንዲህ አለው ፣ “በምድር ላይ አንት የጠየቅከውን አይነት ጥያቄ ጠይቆ የሚያውቅ ሰው የለም ፤ አማልክት ብቻ ይሔንን ያደርጋሉ ፣ እነርሱም በምድር የሚኖሩ አይደሉም፡፡” ንጉሱም በዚህ እጅግ ተበሳጨ፡፡ “እነዚህን ጠቢባን ሁሉ ከባቢሎን ምድር ላይ አጥፋልኝ፡፡” ብሎ አዘዛቸው፡፡



ወታደሮቹ ወደ ዳንኤል ሲመጡ ፣ ለንጉሱ አዛዥ ለአርዮክ እንዲህ አለው፡፡ “ንጉሱ እነዚህን ሁሉ ጠቢባን ማጥፋትን ለምን ፈለገ;” አርዮክም ለዳንኤል በዚያ የተፈጠረውን ነገር ሁሉ ነገረው፡፡ ዳንኤልም ንጉሰን ለማየት ሔደ፡፡ የሕልሙን ትርጓሜ እንዲነግረው ፣ ንጉሱ የተወሰነ ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀው፡፡



ዳንኤልም ወደ ቤቱ ተመለሰና ለወዳጆቹ ለሲድራቅ ፥ ሚሳቅ እና አብድናጎ ሁሉን ነገር ነገራቸው፡፡ ደንኤል ስለ ሕልሙም ሆነ ስለ ፍቺው አንዳች ነገር አያውቅም ነበረ ፥ ነገር ግን ሁሉን ነገር የሚያውቅን አንድ አካል ግን ያውቃል፡፡ ያም አካል እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ስለዚህም ፥ ዳንኤልና ጓደኞቹ ጸለዩ፡፡



እግዚአብሔር ለዳንኤል ሕልሙንና ፍቺውን ገልጦላቸው ነበረ፡፡ ዳንኤልም የሰማይን አምላክ ባረከበ፤ እንዲህም አለ ፣ "የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም የተባረከ ይሁን ፤ ጥበብና ኃይል የእርሱ ናትና፡፡" "ጥበብን የሚገልጥ አምላክ በሰማይ አለ፡፡" ያየውንም ሕልም እና ፍቺ ለንጉሱ ነገረው፡፡



ንጉስ ናቡከደነጾር ሕልሙንና ፍቺውን በሰማ ጊዜ ፣ በዳንኤል ፊት ወደቀና እንዲህ አለ ፣ “ይሄንን ሚስጥር ገልጠሃልና ፣ በእርግጥ ፣ የአንተ አምላክ የአማልክት ሁሉ አምላክ ነው ፤ እንዲሁም የነገስታት ሁሉ ጌታ ፣ እንዲሁም ሚስጢርን ገላጭ፡፡” ከዚያም ንጉሱ ዳንኤልን ታላቅ ሰው አደረገው ፤ ብዙ ታላቅ ስጦታም ሰጠው፡፡ በባቢሎን አውራጃ ሁሉ ላይም ገዢ አደረገው ፤ እናም በሁሉም ጠቢባን ሁሉ ላይ ገዢ አደረገው፡፡



# ምርኮኛው ዳንኤል።

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዳንኤል 1 -2

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16